**የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በኢጣሊያን እና አካባቢው ሀገረ ስብከት ስር በፓሪስ ከተማ የቅዱስ ጊዮርጊስ ዓመታዊ ክብረ በዓል ተከበረ።**

ከመላው ፈረንሣይ ፣ ከቤልጅየም፣ ከጣሊያን በመጡ አበው መነኮሳት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ፣ የደብር አስተዳዳሪዎች፣ ዲያቆናት፣ ሰባኪያነ ወንጌል ፣ እንዲሁም ምእመናን በተገኙበት በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል

ሚያዝያ 24 /2017 (02/05/2025) ከዋዜማው ጀምሮ መርሐግብሩ ጀምሯል ላዕከ ወንጌል መሪጌታ ያሬድ መሪነት ቅኔ ማኅሌቱ በደመቀ ሁኔታ ስብሐተ እግዚአብሔር ሲቀርብበት አድሯል



**ዘቅ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሶበ ተከለለ**

**ደም ወሀሊብ እምነ ከሣዱ ፈልፈለ..** እያሉ ሲያወድሱ አንግተዋል

በነጋታው 25/7/2017 (03/05/2025) ከጠዋቱ 7:00 ላይ በመልአከ ስብሐት ቆሞስ አባ ገብረ ኪዳን መሪነት ሥርዓተ ቅዳሴው ተከናውኗል ፣ በመቀጠልም

**ላዕከ ወንጌል መሪጌታ ያሬድ የዕለቱን ትምህርት "ታማኙ ምስክር" በሚል ራዕ 2፥13 በመጥቀስ በግሩም ሁኔታ አብራርተው አስተምረዋል።**





ላዕከ ወንጌል መሪጌታ ያሬድ

ከትምህርቱ በኋላ የደብሩ አስተዳዳሪ መልዐከ ጽዮን ቆሞስ አባ ወልደ ትንሣኤ ጫኔ ለተሰበሰቡት ሊቃውንት እና ካህናት እንዲሁም ምዕመናን መልእክት አስተላልፈዋል

ቅዱስ ጊዮርጊስ ወ ቁስቋም ማርያም ቤተ ክርስቲያን በፓሪስ ከተማ የራሱ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት ከመንግስት ማዘጋጃ ቤት ቦታ እንደተገዛ ይህንንም የተገዛውን ቦታ ተረክበን በቦታው ላይ ግንባታ መገንባት ለማስጀመር የነበሩትን ሂደቶች አልፈው ዛሬ ላይ የመጨረሻው ምዕራፍ እንደተደረሰ ገልጸው ሲቀጥሉም ይህ የግንባታ ፈቃድ  እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እስከ May 15/2025  የአርቲቴክት ሥራው ሁሉ ታርሞ ያለቀና የተጠናቀቀ ስለሆነ የግንባታ ፈቃድ ለሚሰጠው ቢሮ ሙሉ ዶሴው የሚገባበትና የመሠረት ድንጋይ የምንጥልበትን ሂደት የምንጀምርበት ደረጃ  ላይ እንገኛለን በማለት ገልጸዋል። ከረጅም ጊዜ በኋላ እዚህ ደረጃ የተደረሰው በእናንተ ያላሰለሰ ጥረት በመሆኑ ይህ መልካም ትብብራችሁ እንዳይለይ በማለት  አሳስበዋል ቤተ ክርስቲያኒቷ በአሁን ሰአት ለግንባታ ማስጀመሪያ ገንዘብ ያለን ቢሆንም በቀጣይ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑን በቶሎ ሠርቶ ለመጨረስ የሁሉም አካላት ርብርብ ያስፈልጋል በማለት በሁሉም ነገር ከጎናችን ሆናችሁ ድጋፍ ስታደርጉልን ለነበራችሁ በሙሉ ምስጋና ይገባቹሃል በማለት በቤተ ክርስቲያኑ ስም አመስግነዋል ፣



የደብረ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ወቁስቋም ማርያም ቤተ ክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ

**መልዐከ ጸሐይ ቆሞስ አባ ወልደ ትንሣኤ ጫኔ**

ከዚህ በተጨማሪ **መልዐከ ሕይወት ቆሞስ አባ ጸጋ ዘአብ ባያብል** በፈረንሣይ ያለን ሁላችንም ይህንን ታላቅ መንፈሳዊ ሥራ በጋራ ሆነን ልንሰራ ይገባል ቤተ ክርስቲያን የሁላችንም ናት ይህንን የመሥራት ኃላፊነት አለብን በማለት ለምእመናን መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል በዚሁም ለቤተ ክርስቲያኑ ሕንጻ ማሰሪያ የሚሆን የገቢ ማሰባሰቢያ አድርገዋል ።





በመጨረሻም ታቦተ ሕጉ ከመንበረ ክብሩ ተነሥቶ በሊቃውንቱ እና በካህናቱ እንዲሁም በሰንበት ት/ቤት መዘምራን ታጅቦ ዑደት አድርጓል የሰንበት ተማሪዎችም ያሬዳዊ ወረብ አቅርበው ታቦቱ ወደ መንበረ ክብሩ ተመልሷል።









ከዋዜማው ምሽቱ 21 ጀምሮ የነበረው ክብረ በዓል ከቀኑ 12;30 ላይ ተጠናቋል

ሕዝበ ክርስቲያኑም የተዘጋጀውን ማዕድ ቀምሰው ወደ ባዕታቸው ተመልሰዋል።

አምላከ ቅዱስ ጊዮርጊስ ስሙ ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን

ለሀገረ ስብከቱ ዘገባው ያደረሰው መ/ር እስክንድር ፈረንሣይ ፓሪስ